የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት
www.gonderhibret.org Gonder Hibret for Ethiopian Unity Email: gonderhibret@gmail.com

27/07/2018

# ኢትዮጵያ በተከታታይ ቀናት ሁለት ድንቅ ልጆቿን አጣች!

በኢትዮጵያ አገራችን የተከፈተው የለውጥ ተስፋ ገና ብዙ ቀናትን አላስቆጠረም። በሰላም ውለን ገብተናል የሚለው ጊዚያዊ ተስፋ እውን እየሆነ ሳይሆን ይልቁንም ጊዜው ወደየትኛው አቅጣጫ እየወሰደን እንዳለ መተምበይ እጅግ አስቸጋሪ ሆኗል። ከሰኔ 16 ቱ የቦምብ ፍንዳታ በኋላ በተለይ በአዲስ አበባችን ትምህርት አግኝተን የደህንነትና የፖለስ ኃይል ልዩ ትኩረት አግኝቶ ለለውጥ የቆሙ ወገኖቻችንን ከአደጋ መከላከል ተችሎ ይሆናል ብለን እንገምት ነበር።

ዛሬ ግን ያየነው ከገመትነው ውጭ ነው! ትላንት የሰውን ህይወትና የአገራችን አንጡራ ኃብት ሲያሚጥጡ የነበሩ፤ ከምዝበራ እጃቸው ሲቆረጥ፤ የመዘበሩትም እንዳይጋለጥ የንጹህ ዜጎችን ህይወት መቅጠፍ ጀምረዋል።

የኢንጅነር ስመኘው በቀለ የግፍ ግድያ የዚሁ የግፈኞአች አጥፍቶ መጥፋት ቀጣይ እቅድ የመጀመሪያው ምዕራፍ መሆኑ ነው። ደረቅ በልቶ ጉሮሮውን አድርቆ አንጀቱን አስሮ በታላቅ ውጤት ትምህርቱን አጠናቆ አገሩን ለረዥም ዓመታት ያገለገለው ወንድማችን በነዚህ ግፈኞች እጅ መውደቁ የበለጠ ታሪኩ ከመሬት በላይ ገዝፎ እንዲኖር ቢያደርገው እንጂ እንደ ሥጋና አጥንቱ መሬት በታች ተቀብሮ የሚቀር አይደለም።

የኢንጅነር ስመኘው ሞት የግፈኞችን ህይወት ፈጽሞ አይቀጥልም። የሕዝብን ይቅርታ የናቁት ጠላቶቻችን የግፍ በትራቸውን በሰነዘሩብን ቁጥር እኛም አምረን እንደምንታገል ቢረዱ ኖሮ ይህችን የተሰጠቻቸውን ወርቃማ ጊዜ መልሰው ባላጨለሙ ነበር።

በመሆኑም፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ እያየ ያለውን የለውጥ ተስፋ ለፍሬ ለማብቃት ከመቸውም በበለጠ ጠንክሮ ሊደራጅና የለውጡ ዘብ መሆን ይጠበቅበታል። በአንድ ኢንጂነር ስመኘው ህልፈት ሺዎችን በመተካት የአረመኔዎችን አጉል ቅዥት በማክሸፍ መልካም ጅምራችንን ከዳር እናድርስ። የአባይ ግድብ ሲወሳ የኢንጅነር ስመኘው ህያው ታሪክ ይወደሳል፤ ጅምሩም ዳር ይደርሳል።

በተመሳሳይ መልኩ በትናንትናው ዕለት እዚህ ሰሜን አሜሪካ ለተወሰነ ጊዜ ህክምናቸውን ይከታተሉ የነበሩትን የአማራው ክልል መሥተዳደር የጽ/ቤት ኃላፊ የነበሩትን አቶ ተሥፋየ ጌታቸውን እ. ኤ. አ (07/25/18) አጥተናል። ይህም ኢንጅነር ስመኘው ከመሞቱ አንድ ቀን ቀድሞ መሆኑ ነው። አቶ ተስፋየን ያወቅናቸው ምንም አጭር ጊዜ ቢሆንም፤ እጅግ ደግና የሰውን ኃሳብ የሚያዳምጡ፤ አገራችንን ከነበረችበት ውስብስብ የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ለማላቀቅ ቆርጠው ከተነሱት ከሥር ዓቱ ጋር ከነበሩ ለውጥ አራማጆች አንዱ እንደነበሩ በሙሉ ድፍረት መመሥከር ችለናል።

አቶ ተስፋየ ረቡዕ ለቀዶ ጥገና ሊገቡ ማክሰኞ ዕለት የህዝባቸውንና የአገራቸውን ጉዳይ ይመለከተናል ከሚሉ ወገኖች ጋር በሰሜን አመሪካ በክቡር ዶ/ር አብይና በክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ቡድን የሥራ ጉብኝት ዙሪያ ሲመክሩ መርኃ ግብር ሲያዘጋጁ ነበር ያመሹት። የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት እንዲህ አይነት ሰዎችን በተከታታይ ቀናቶች ማጣት ለመላ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለሚወዱ የተጀመረው የለውጥ ተሥፋ እውን ሆኖ ማየት ለሚሹ ዜጎቻችን ሁሉ መራር ኃዘን መሆኑን ይገነዘባል።

በመሆኑም የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት ለኢንጅነር ስመኘው በቀለ እና ለአቶ ተሥፋየ ጌታቸው የቅርብ ቤተሰቦቻቸው፤ ጓደኞቻቸውና ለመለው የኢትዮጵያ ሕዝብ መፅናናትን ይመኛል።

የሁለቱንም ወገኖቻችን ህልፈተ ህይወት እግዚአብሔር አምላክ በአፀደ ነፍስ በሰላም ያስቀምጥልን ዘንድ እንመኛለን!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት።